# አሲምባ ርዕስ አንቀጽ

Editor’s Note ቁጥር 3/2010


## አስቀድሞ ምስጋና ለኋላ ሃሜታ ያስቸግራል!

### “ዶ/ር ኮለኔል ዓቢይ አሕመድ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስቴር የለውጥ ሐዋርያ ስለሆነ ሁላችንም ልንደግፈው ይገባል! ተደመሩ” ለሚሉን የባሕር ዳሯ ወ/ሮ እማዋይሽ እንዳለችው የሽግግር መንግሥት ይቋቋም ሳሆን በተቀደለልን ቦይ እንፍሰስ ነው? ተጠራጣሪ ቶማሶችን ዕውነተኛ ለውጥ ፈላጊዎች አይደሉም የሚለን ማነው?

የኢትዮጵያ ሕዝብ ላለፉት 27 ዓመታት ራሱን ከወያኔ ሥርዓት ለማላቀቅ ባደረገው ትግል ከፍተኛ መስዋዕትነትን ከፍሎ ዛሬ ወያኔ እንደፈለገው ሊገዛ ያልቻለበት ሁኔታ ላይ አድርሶታል። የኃይል ሚዛኑም በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ወደ ሕዝቡ፣ ወደ ኢትዮጵያዊነት እያጋደለ ያለበት ሁኔታን አመላካች የሆኑ ምልክቶችንም እያየን ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ወያኔ ከ 27 ዓመታት በፊት በምዕራባውያን የጡት አባቶቹ እርዳታ በአፄ ምኒሊክ ቤተ-መንግሥት ከገባ በኋላ ጠፍጥፎ በሠራው መዋቅር ላይ የተከለው የዘረኞች (አፓርታይድ) ሥርዓት በሀገራችን ከጫፍ እስከጫፍ የተጠላ ሆኗል። ያም ብቻ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ የዘረኝነትን ፖለቲካ ክሥረት ጠንቅቆ የተረዳበትና አንቅሮ የተፋው እንደሆነም ለሁሉም ግልጽ ሆኗል።

ሕዝቡ በአብሮነትና በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ያካሄደው ትግል በወያኔ ላይ ያደረሰው ውጥረት ወያኔን (ሕወሓትን ) በመካከሉ መከፋፈልን ስላመጣበት በተፈጠረው ክፍተት የተለያዩ ኃይሎች ዕድሉን ተጠቅመው ራሳቸውን ወደ ሥልጣን ኮርቻ ለማንጠልጠል ሲፍጨረጨሩ የምናይበት ወቅት ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ወያኔ ባምሳሉ ጠፍጥፎ ሠርቶ ለሽፋን ሲጠቀምባቸው የነበሩ እንደ በአዴን፣ ኦሕዴድ… የመሳሰሉ ተለጣፊ፣ ታዛዥና አሻንጉሊት ድርጅቶች፣ የልብ ልብ ተሰምቷቸው የሥልጣን ተራው የኛ ነው! ብለው በሥልጣን ፉክቻው ያለ የሌለ ኃይላቸውን ተጠቅመው እየተወገረገሩ እንደሆነ ግልጽ ነው። ለዚህ ደግሞ ላለፉት 27 ዓመታት የሄዱበት የዘር ፖለቲካ መክሰሩንና እንደማያዋጣቸው አሁን ስለተረዱ የሕዝቡን የአብሮነት ጥያቄ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ አድርገውና የሕዝቡን ድምጽ ነጥቀው የሚጮኹበትን ጊዜ አምጥቷል። የአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ኢትዮጵያዊነትን ማቀፍ በድንገት የተከሰተ ዱብ ዕዳ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት ላይ የተሸረበው የክልል (አፓርታይድ) ሥርዓት በሕዝባዊው ዓመጽ በደረሰበት ምት ቆስሎ እየተውገረገረ እንደሆን አመላካች ምልክት ነው። ከሁሉም በላይ መጠንቀቅ ያለብን አንዳንድ የዋሆች እንደሚነግሩን ወያኔ የተከለብን ሥርዓት ቆስሎ እንደሁ እንጀ ሞቷል ልንል በፍጹም እንደማንችል ነው።

ዛሬ ሀገር ወዳዶች ከምን ጊዜውም የበለጠ ፍቅሬ ፍቅሬ በዝቶ ባልተጨበጠ ተስፋ ሁሉም ተሳክሮ ባለበት ወቅት የሕዝብ ትግል ፍሬ ለሦሥተኛ ጊዜ እንዳይሠረቅ በተጠንቀቅ የምንቆምበት ወቅት ነው። የትግላችን መጨረሻ መቋጫው የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት የሚያደርግ፣ በሀገራችን ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረቱ የሚጣልበት፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በሕግ ፊት እኩል የሚሆንበት፣ የመናገር፣ የመሰበሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ በነፃ የመደራጀትና ሰብዓዊ መብቶች በሙሉ ሳይሸራረፉ

ካለምንም ገደብ የሚከበርባት ሀገር የሚያደርግ ሥርዓት ለማምጣት ምን ማድረግ አለብን ብለን ሁላችንም በጥሞና የምንመክርበት ወቅት እንጂ በሚወረወርልን አጫጭር መፈክር የመደመር የመቀነስ ጉንጭ አልፋ ንትርክ ውስጥ ገብተን ጎራ የምንለይበት ጊዜ ሊሆን አይገባም። በአንድ ግለ-ሰብ ዙሪያም ተኮልኩለን እንደግፈው ወይም አንደግፈው በሚል ንትርክ ጊዜ ልናጠፋም አይገባንም። በዲያስፓራ ያሉ የተለያዩ ድረ-ገጾች፣ የፖለቲካ ስብስቦች፣ የኃይማኖት ተቋማት ሳይቀሩ አዲሱን ጠ/ሚኒስቴር ያልደገፈ ሕዝቡ የጠየቀውን ለውጥ የሚጻረር፣ የማርያም ጠላት ዓይነት አድርጎ ስሜታዊ ክርክር ውስጥ ባንገባም ቢያንስ ተጠራጣሪ ቶማስነታችንን ብናስመዘግብ በሀገራችን የሚመጣው ለውጥ አስተማማኝ እንዲሆን ካለን ጽኑ ፍላጎት እንደሆነ እንዲታወቅልን እንሻለን። ባለፉት 40 ዓመታት የተነጠቁ የሕዝብ ትግል ፍሬዎችን ለመታዘብ የዕድሜ ዕውቀቱን የተቸርንና የበቃን ስለሆነም ጥርጣሬአችንን ሀገር ወዳዶች ይገነዘቡልናል ባዮች ነን።

ለምሳሌ አንዳነዶች "በኢትዮጵያ የተከሰተው የለውጥ ሂደት ባልተጠበቀ መንገድ ተጀምሮ በፈጣን ግስጋሴ እየተጓዘ ይገኛል" ይሉና "በህዝቡ መሃል አንጻራዊ ሰላም ሰፍኗል።" "በዘውጌዎች መሃል የነበረው ጥላቻ እረግቧል።" "በሃይማኖቶች መሃል የነበረው ክፍፍል ወደ አንድ እየመጣ ነው።" "ዕስር ቤቶች አምቀዋቸው የነበሩትን እስረኞች ነጻ እንዲወጡ የበሮቻቸውን ቁልፍ ፈትተዋል።" "አፋኝ ህግጋት ተሽረዋል።" "የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተነስቷል።" "ዘረኝነት ሀዘን ለሀዘን ተቀምጧል።" "የዜጎች ሰብአዊ መብቶች መከበር ጀምረዋል።" "ይቅርታና መደመር የገሪቱ የፖለቲካ አግማስ ሆነዋል።" "ፍቅርና ሰላም በተስፋይቱ መሬት ችግኞቻቸውን ተክለዋል።" ወዘተ..... ወዘተ.... ይሉና ማጠቃለያቸውን ከሞላ ጎደል "ዶ/ር አቢይ ወደ ስልጣን በመጡ መቶ ቀናት ውስጥ ዕውን ይሆናሉ ተብለው የማይታሰቡ ክንውኖች ተከናውነዋል።" በቅርቡ ደግሞ "የኢርትራ ሕዝብም ከኢትዮጵያ ጋር ተደምሯል" ይሉናል። ባጭሩ በሃገር ቤትም ሆነ በዲያስፓራ አዲሱን ጠ/ሚኒስቴር እንደግፍ ግርግሩ ተሟሙቋል።

እንግዲህ ከላይ በጥቅስ ውስጥ የተቀመጡትንና ሌሎችንም ነጥብ በነጥብ አንስተን መመርመር የዚህ ርዕሰ-አንቀጽ ዓላማው አይደለምና ይሄንን ሁሉ ለውጥ ያመጣልን ተብሎ የመለኮታዊ ኃይል የሰጠነው ጠ/ሚኒስቴር ማነው የመረጠው? ብለን ብንጠይቅ መልሱ **ኢሕአዴግ** ነው የሚሆነው። **ኢሕአዴግ** ደግሞ 99 ከመቶ አቸንፈናል የሚሉ በማጭበርበር ተቃዋሚዎችን አጥፍተው (በየእሥር ቡቱ አንገላተው፣ ገድለው...ወዘተ.) በምርጫ ስም በሥልጣን ራሳቸውን ያስቀመጡ ቡድኖች መሆናቸውን አንርሳ (ምክር ቡቱንም ጨምሮ ማለት ነው)። ስለሆነም ሰውየውንም የኢትዮጵያ ሕዝብ የመረጠው ስላልሆነ ነገ ጧት የመረጡት ቡድኖች ዘብጥያ ሊያወርዱት ይችላሉ ማለት ነው። ሌላው ደግሞ የሚንቀሳቀሰው **ኢሕአዴግ** ባወጣለት ህግና ሥርዓት ስለሆነ ወደድንም ጠላን ሰውየው ሀገሪቱን ሊመራ የሚችለው አሁንም የወያኔዎቹን የክልል (አፓርታይድ) ሥርዓት በሚሰጠው ህገ-መንግሥት ነው።

በነገራችን ላይ ሁሉም የፖለቲካ እሥረኞች እስካልተፈቱ ድረስ፣ አንድ ሰው እንኳ በፖለቲካ አመላካከቱ እስከ ታሠረ ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ እሥረኞች ተፈተዋል ብለን አፋችንን ሞልተን መናገር በጣም ያሳፍራል። በአሲምባ **በኩል ሁሉም የፖለቲካ እሥረኞች ካለምን ቅድመ ሁናቴ አሁኑኑ ይፈቱ!** መፈክራችን ነው። ለመሆኑ በኢሕአፓነታቸው ደብዛቸው ስለጠፉት ወገኖችስ ዝምታችን ለምን ይሆን? እንግዲህ መብት በሽበሽ ነው ብለው ተደመሩ! እያሉ የሚወተውቱን ወገኖች ለዚህም መልስ

# አሲምባ ርዕሰ አንቀጽ

Editor's Note ቁጥር 3/2010

ቢሰጡን መልካም ነው። የዜጎች ሰብአዊ መብቶች ቢከበሩማ ኖሮ በትንሹ የኤርትራው መሪ አዲስ አበባ ሲገባ ከፍተኛ አቀባበል ተደረገለት የተባለውን ያክል፣ የኢትዮጵያን ባንዲራ አንግበው ይሄንን ዘረኛ ጠባብ በሀገራችን ኢትዮጵያ ላይ ላደረሰው ጥፋትና በባድሜ ከ100 ሺህ በላይ ለወደቁ ወገኖቻችን፣ በዚያ አላስፈላጊ ጦርነት አካላቸው ጎድሎ የሚንከራተቱ ወገኖች ከየማዕዘኑ ወጥተው ተቃውሞ ሠልፍ ባደረጉ ነበር። አሰብ የኢትዮጵያ ናት! ኤርትራና ኢትዮጵያ አንድ ሕዝብ ነው! የሚሉና ሌሎችም ድምጾች በተሰሙ ነበር። በባሕር ዳር የሕዝብ ድጋፍ ሰልፍ ላይ እማዋይሽ ያነሳችው ጥያቄ የሽግግር መንግሥት ሊቋቋም ነው? ወይስ በተቀደደልን ቦይ ልንፈስ ነው? ያለችው በኢቲቪ ተቆርጦ ባልወጣ ነበር። እንግዲህ የሰብዓዊ መብት እኮ የመደገፍና የመደመር ብቻ ሳይሆን ጥቂትም ቢሆኑ የመቃወም፣ ጥያቄ የማንሳት፣ ማብራሪያ መጠየቅም ሆነ ሌሎችንም ሰብዓዊ መብቶች የሚረጋገጥበት መሆኑን ለማመላከት ነው።

ለማጠቃለል፥

ወያኔ በ 27 ዓመት ውስጥ በኢትዮጵያ ላይ የመጣ መዓት ሆኖ ቀጥቅጦ የገዛ መሆኑን የምናውቅና በተለያየ ጊዜያት ሕዝቡ እምቢተኝነትን ያሳየባቸውን ሕዝባዊ ዓመጾች ያኮላሸባቸውና ራሱን በሥልጣን ኮርቻው ላይ መልሶ ያደላደለባቸውን ታሪካዊ ስልቶችና ዘዴዎች በቅጡ ላጤንን አዲሱ ጠ/ሚኒስቴር ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ! ብሏል ብለን እንደ አያሌ የዋህ ሀገር ወዳዶች ዳንኪራ ልንጨፍር አይጠበቅብንም። ይልቁንስ ተጠራጣሪ ቶማሶች ሆነን ከባድ ጥያቄዎችን በማንሳት ከምን ጊዜውም የበለጠ የሕዝቡ ትግል ፍሬ በድል አጥቢያ አርበኞች እንዳይበላ መከላከል የሁሉም ሀገር ወዳዶች ተግባር መሆን ይገባዋል። በልተጨበጠ ባዶ ተስፋ ተወጥረን ባለመጨፈራችን የሕዝቡን የለውጥ እንቅስቃሴ እንደምንቃወም መደረጉ የማያስፈልግ ትንንቅን በሕዝባዊው ወገን ውስጥ ማጫርና በግርግር ወደ ሥልጣን ለሚመጡ ቆራጭ ፈላጮች መመቻቸትን መምረጥ ነው እንላለን።

ሕዝቡ የተዋደቀበትን ኢትዮጵያዊነትና አብሮነትን መፈክር በማንሳት ሁሉንም ባይሆን ጥቂት የፖለቲካ እስረኞችን ፈቷልና እንደግፈው የሚለው ጩኸት በዝቶ በጥርጣሬ የምንጠይቀውንም በደፈናው ጨፍልቆ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል አቸናፊነት እንደምንቃወም በመፈረጅ፤ ረጋ ያለ የሀገሪቱን ሁናቴ የመገምገምና በምን ዓይነት መንገድ ሥልጣን ወደ ሕዝብ ሊገባ ይችላል የሚሉትን ነጥቦች ለመወያየት እንዳይቻል ዝም የማሰኘቱ ጫጫታ እንዳይሆን እንፈራለን። <u>አምባገነን ሥርዓትን አውርዶ ሕዝባዊ ሥርዓትን ለመመሥረት የግድ የሽግግር መንግሥት ሊመሠረት</u> ሲገባ ከወዲሁ የሕዝቡን ድምጽ እየዘመሩ ያሉ የትላንት ከሃዲዎችና ችግር ፈጣሪዎች አዲሱ መሪ ባዘጋጀላቸው ቴያትር ለመሳተፍ፤ ብሎም የአንደኛ ማዕረግ መቀመጫቸውን ለመያዝ ሲሯሯጡ ለታዘብን፤ የኢትዮጵያን የቅርብ ጊዜ የትግል ታሪክ ጠንቅቀን ለምናውቅ እጃችንን አጣጥፈን ልንቀመጥ በፍጹም አይታለንም።

ኢትዮጵያችን ዴሞክራሲያዊት እንድትሆን በመመኘትና የተስፋ ዳቦ የናኘን አንድ ግለ-ሰብ ብቻ ካላቀፋችሁ አሁንም ለሦሥተኛ ጊዜ የሕዝቡን ትግል ውጤት ማስበላት ነው የሚሆነው። ለምን ቢባል ወያኔ የተከለው ሥርዓት በቦታው ታትሞ ያለ ስለሆነ ማለት ነው። የሚያስፈልገው የወያኔን ሥርዓት በሕዝባዊ ሥርዓት መቀየር ነው! ለዚህ ደግሞ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር

መሰባሰብ፣ መደራጀትን ይጠይቃል። ያንን ማድረግ ካልቻልን ደግሞ እንደ ኢሕአፓ ያሉ እያታገሉ ያሉ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችን መቀላቀልና ከሕዝቡ ወገን መደመር ሌላው አማራጭ ነው።

ጥያቄው መሆን ያለበት ከማን ጋር ነው የምንደመረው? ሕዝቡን የሥልጣኑ ባለቤት ከሚያደርገው ወገን ወይንስ በግለ-ሰቦች ዙሪያ ተኮልኩለን በተደጋጋሚ እንደሆነው የማይሆን ዕምነት ጥለንባቸው በይፋ ለሚከዱን በተስፋ ለሚነዱን ሰለባ መሆን? ሌላውን ብንተወው ባለፉት 27 ዓመታት ሕዝባዊ ትግል ውስጥ እንኳ በመሪነት ከመካከላችን መርጠን ሳይሆን በስሜት ብቻ ራሳቸውን ማንዴላ ያሉን ወገኖች ዛሬ ይት ነው ያሉት? ብለን ብንጠይቅ “አስቀድሞ ምስጋና ለኋላ ሃሜታ ያስቸግራል” የሚለውን የወገን ተረት በግልጽ ትምህርት የሰጠናል። እናም አዲሱ ጠ/ሚኒስቴር ከሕዝብ ወገን መደመር ከፈለገ እነሆ ፈረሱም ይሄው! ሜዳውም ይሄው! በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ስለሀገራችን ያገባናል የሚሉና ሕዝቡም ከየአካባቢው በሚመረጣቸው አማካሪዎች የሽግግር መንግሥት አሁኑኑ! እንዲያውም ሰውየው በአሁኑ ጊዜ ባለው ታዋቂነትና ድጋፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ መልሶ ይመርጠዋልም ብለን እንገምታለን። እናም የባሕር ዳሯ ወ/ሮ እማዋይሽ ላቀረበችው ጥያቄ የሽግግር መንግሥት ወይንስ በተቀደደልን ቦይ መፍሰስ? ምልሳችን የማያጠራጥር የሽግግር መንግሥት አሁኑኑ! ይሆናል።

የሽግግር መንግሥት አሁኑኑ!

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያብባል!

የአሲምባ ድረ ገጽ ዝግጅት ክፍል - (ሐምሌ 14, 2010)